ከ ፋለኝ ዓለሙ ና ተባባሪዎቹ ከገደሏቸው የከ15 ሰማዕታት ጥቂቶቹ

# ለዴንቨርና አካባቢው ወገኖች





በሀገራችን ኢትዮጵያ በ1968/70ዎቹ አንድ ትውልድ በመመተር በሚታወቀው የደርግ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ተዋንያን የነበረው የከፍተኛ 15ቱ ቀይ ሽብር ኮሚቴ አባል በመሆን በርካታ ወጣቶችንና ጎልማሶችን በመግደልና በማሰቃየት የሚታወቀው ከፋለኝ ዓለሙ በቅርቡ August 24, 2012 በሰሜን አሜሪካ (ሰ.አ.) ዴንቨር ጸጥታ ኃይሎች በጥርጣሬ ተይዞ በምርመራ ላይ ይገኛል።

በዴንቨርና አካባቢው እንዲሁም በሰ.አ. በተለያየ አካባቢ ባሉ የጊዜው ሰለባዎችና በአጋጣሚ በሕይወት የተረፉ የዚያ ጊዜ ወጣቶች ከፋለኝ ዓለሙን በመከታተልና በማስታወስ ያደረገውን ድርጊት ምስክርነት በመስጠት ከዛሬ አንድ ዓመት ከስድስት ወር በፊት በጀመሩት ክትትል ተጠርጣሪው ለእሥር ሊዳረግ በቅቷል።

የዚህን አረመኔ ግለሰብ በሕዝብ ልጆች ላይ ያደረሰውን በደልና ግፍ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ለማሳወቅ በማቀዳችን ፈቃደኞች ለሆናችሁ ወገኖች በዴንቨር ከተማ ስብሰባ አዘጋጅተናል።

በከፋለኝ ዓለሙ ቀጥተኛ ተጠቂ የነበሩ ግለሰቦችና ያደረገውንና የሠራውን ግፍ የሚያውቁ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉና ወደ ስብሰባው በመምጣት ትከታተሉና ያላችሁን ጥያቄና አስተያየት ትሰጡ ዘንድ በአክብሮት እንጋብዛለን።

## የምሥክርነት ሕዝባዊ ስብሰባ
## ከፋለኝ ዓለሙ ማነው?

ቀን : ዕሁድ September 30, 2012
ሰዓት : ከቀኑ 2:00 pm ጀምሮ
ቦታ : ዴንቨር
አድራሻ: Selam Ethiopian Restaurant
1030 Havana St,
Aurora, Co 80010

ከ1968/70ዎቹ የደርግ ቀይ ሽብር በሕይወት ያሉና የስነልቦና ጥቃት ሰለባ ለሆኑ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነፃ የማማከር አገልግሎት በዴንቨር መዘጋጀቱን አስመልክቶ ገለጻ ይደረጋል።






## "ያ ትውልድ ተቋምን" እናስተዋውቃችሁ

በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ እውቅና ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ያለው "ያ ትውልድ ተቋም" በ July 06, 2012 በዳላስ ከተማ እራሱን ይፋ ማድረጉና መሥራች ጉባዔውን ማካሄዱ ይታወቃል። ቀደም በማለትም "ያ ትውልድ ተቋም" በ May 01, 2012 (በሜይ ዴይ) (ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም.) ወደ ሦስት ሺህ የሚጠጉ የዚያን ትውልድ ሰማዕታት ስምና ፎቶ ያካተተና የቀድሞ ሰነዶችን የያዘ www.yatewlid.com ወይም www.yatewlid.org ድረ ገጽ ለሕዝብ ይፋ አድርጓል። በመሆኑም የ "ያ ትውልድ ተቋም" ን ዓላማ፣ ተልዕኮና ራዕይ በተመለከተ ገለጻና ማብራሪያ የዝግጅቱ አንዱ ክፍል ስለሚሆን መጥታችሁ ትከታተሉ ዘንድ በአክብሮት ተጋብዛችኋል።



ያ ትውልድ ተቋምን በመተባበር

- የመረጃ ምንጭ ይሁኑ
- ለትውልዱ መታሰቢያ ያኑሩ
- የተጎዱ ወገኖችን ይርዱ

ከቅጽ 1 - 38 የዴሞክራሲያ ዕትሞችና ሌሎች የሚገኙበት

